የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ.፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 26
ADDIS ABABA ,4th March, 2025

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፷፰/፪ሺ.፲፯

የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ እና የመከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………….ገጽ ፲፯ሺ.፯፻፳፩

## Content

REGULATION NO.568/2025

Defense Specialized Referral Hospital Group and Defense Diagnostic Center establishment Regulation…………………………… Page 17721

**ደንብ ቁጥር ፭፻፷፰/፪ሺ.፲፯**

**የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ እና የመከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፫፻፲፬/ ፪ሺ.፲፮ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና አንቀፅ ፵፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ እና የመከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፷፰/ ፪ሺ.፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**REGULATION No. 568/2025**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF DEFENSE SPECIALIZED REFERRAL HOSPITAL GROUP AND DEFENSE DIAGNOSTIC CENTER**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Sub-Article (1) of Article 6 and Sub-Article (1) of Article 47 of the Federal Government Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024.

**PART ONE**

**General**

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "Defense Specialized Referral Hospital Group and Defense Diagnostic Center establishment Council of Ministers Regulation No. 568/2025".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ **"አዋጅ"** ማለት በፌደራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬ / ፪ሺ፲፮ ነው፤

፪/ **"ልዕለ ህክምና አገልግሎት"** ማለት ሆስፒታሉ ልዩ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራባቸው የተመረጡ ስፔሻሊቲ፣ ሰብ ስፔሻሊቲ እና ሱፐር ስፔሻሊቲ አገልግሎቶች ነዉ፤

፫/ **"ተቀጥላ ተቋም"** ማለት ንብረትነቱ ሙሉ ለሙሉ የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ አባል የሆነ ወይም የመከላከያ ጤና ግሩፕ ባላክሲዮን የሆነበት እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በግሩፑ ቁጥጥር የሚደረግበት ድርጅት ወይም ኩባንያ ነው፤

፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፫. ዓላማ

በዚህ ደንብ የተቋቋሙት ተቋማት የሚከተሉት ዓላማ ይኖራቸዋል፡-

፩/ ጥራት ያለው እና ደረጃውን የጠበቀ የሆስፒታል አስተዳደር፣ የህክምና መሳሪያና የሰው ኃይል በማደራጀት የሀገሪቱን የልዕለ ህክምና፣ የዲያግኖስቲክ እና ተዛማጅ አገልግሎት ፍላጎትን ማሟላት፤

፪/ የተሻለ ህክምና ፍለጋ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ ታካሚዎች በሀገር ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

## 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "**Proclamation**" means the Federal Government - Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024;

2/ "**Super specialty medical service**" means selected specialty, sub-specialty and super specialty services of the hospital;

3/ "**Subsidiary**" Means Company owned by Defence Specialized Referral Hospital Group individually, or company in which Defence Specialized Referral Hospital Group is a shareholder with other parties and maintains direct or indirect control ;

4/ "**Person**" means natural or juridical person;

5/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Objectives

The institutions established by this Regulation shall have the following objectives:

1/ To meet the country's need for ,super specialty medical, diagnostic and related services by organizing advanced and standardized hospital management, medical equipment and human resources;

2/ To ensure the accessibility of better medical treatment in the country to minimize travels to abroad for such service.

## ክፍል ሁለት
## ስለመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ እና ስለመከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከል

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ስለመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ

**፬. መቋቋም**

፩/ የመከላከያ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ግሩፕ ከዚህ በኋላ "ግሩፕ" እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ግሩፑ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮ መሰረት ይተዳደራል፡፡

፫/ ግሩፑ የመከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከልን ጨምሮ ሌሎች በስሩ የሚቋቋሙ ተቀጥላ ተቋማትን የሚያስተዳድር ይሆናል፡፡

**፭. ተጠሪነት**

ግሩፑ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል።

**፮. ዋና መስሪያ ቤት**

የግሩፑ ዋና መስሪያ ቤት ቢሾፍቱ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም የሀገሪቱ ክፍል ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፯. የግሩፑ ተግባርና ኃላፊነት**

በአዋጁ ለመንግስት የልማት ድርጅት የተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ግሩፑ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ግሩፑ እና ተቀጥላ ተቋማቱ ዘመኑ የደረሰበትን የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

## PART TWO
## DEFENCE SPECIALIZED REFERRAL HOSPITAL GROUP AND DEFENCE DIAGNOSTIC CENTER

## SUB SECTION ONE
## DEFENCE SPECIALIZED REFERRAL HOSPITAL GROUP

4. **Establishment**

1/ Defense Specialized Referral Hospital Group hereinafter referred to as "The Group" is hereby established by this Regulation as a Federal Public Enterprise.

2/ The Group shall be governed by the Federal Government-Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024.

3/ The Group shall Administers Defense Diagnostic Center and other Subsidiaries that will be established under its pool.

5. **Supervising Authority**

The Federal Democratic Republic of Ethiopian Ministry of Defence shall be the supervising authority of the group.

6. **Head Office**

The Group shall have its Head Office in Bishoftu, and may open branches in other parts of the country as may be necessary.

7. **Duty And Responsibilities of The Group**

Without prejudice to the duties and responsibilities of Public Enterprise provided in the Proclamation, the Group shall have the following duties and responsibilities:

1/ To ensure that the group and its subsidiaries provide advanced healthcare services;

፪/ ግሩፑ እና ተቀጥላ ተቋማቱ ተልዕኮዎቻቸውን ለመወጣት የሚያስፈልጋቸውን ሀብት በማሟላት መደገፍ፤

፫/ ተቀጥላ ተቋማትን ማቋቋም፣ ነባር ተቋማትን ወደ ግሩፑ መቀላቀልና አባል ተቋማትን ማሰናበት፤

፬/ የገበያ መርህን እና ዓለማቀፍ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን መቅጠር፣ ክፍያ እና ማበረታቻዎችን መወሰን፤

፭/ ግሩፑ እና ተቀጥላ ተቋማቱ ከውጭ ሀገር ለሚገዟቸው እንዲሁም ለሚሸጧቸው እቃዎች እና አገልግሎቶች በውጪ ምንዛሬ የመክፈል እና የማስከፈል፤

፮/ በሀገር ውስጥ ገበያ የማይገኙ ለግሩፑና ተቀጥላ ተቋማቱ ተግባር የሚውሉ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን በቀጥታ ከውጭ ገዝቶ ማስገባት፤

፯/ ህክምና ነክ ወይም ህክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለሶስተኛ ወገን እንዲተላለፍ የሚቀርብ ጥያቄን መርምሮ ለተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፰/ የግሩፑን ተልዕኮ እና ፍላጎት ለማሳካት ሀገራዊ፣ ቀጠናዊ እና አለማቀፋዊ ከሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር አጋርነትን መመስረት፣ የሚሰጡ ድጋፎችን መቀበል፤

፱/ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ምንጮች ገንዘብ ያሰባስባል፤

፲/ እንደ አስፈላጊነቱ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተቀጥላዎች መያዣ ወይም ዋስትና የመስጠት፤

2/ Provide the Group and its subsidiaries, with adequate resources to support its purposes;

3/ Establish or Incorporate a new companies that can be included in the Group or dismiss member companies;

4/ Employ appropriate staff, determine their payment and incentives in accordance with commercial principles and international best practice;

5/ Pay and charge in foreign currency for the goods and services that the Group and its subsidiaries buy and sell from abroad;

6/ Buy and import goods and services that are not available in the domestic market for the group and its subsidiaries;

7/ Examines and recommend the supervising authority to approve requests from other entities to transfer all or part of medical or non-medical services to a third party;

8/ Establish national, regional and international partnerships with governmental and non-governmental entities in the interest of the Group to full fill its objectives, accepting the support they provide;

9/ Raise money from local and foreign source;

10/ Enter into any guarantee indemnity or suretyship to any of its subsidiaries and charge it deemed necessary;

፲፩/ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ፣ የመከራየት፣ የማከራየት፣ እና የመጠቀም፤

፲፪/ የኢንቨስትመንት አዋጭነትን፣ የካፒታል መጠን እና የሽርክና ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት፤

፲፫/ ግሩፑ ከተቀጥላ ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በተመለከተ በንግድ ሕጉ የተቀመጡ መርሆችን መሰረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፬/ የተቋቋመበትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

፰. <u>**ካፒታል**</u>

የግሩፑ የካፒታል መጠን ብር ፹ ቢሊዮን (ሰማንያ ቢሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፳ ቢሊዮን (ሃያ ቢሊዮን) በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፱. <u>**ሀላፊነት**</u>

ግሩፑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆኑም፡፡

፲. <u>**የሂሳብ ዓመት**</u>

የግሩፑ የሂሳብ ዓመት የኢትዮጵያ መንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን ከሐምሌ አንድ ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ሠላሳ ቀን የሚቆጠር ይሆናል፡፡

፲፩. <u>**የሂሳብ መዝገብ አያያዝ**</u>

የግሩፑ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና ኦዲትን በተመለከተ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ መሰረት ይመራል፡፡

11/ Purchase, sell, rent, lease, and utilize immovable and movable asset properties;

12/ Investigate and make decisions on the investment feasibility, capital levels, and partnership issues;

13/ Based on the principles of the commercial code, the Group will develop a procedure regarding the relationship with the subsidiary institutions;

14/ To engage in any other related activities as are necessary for the attainment of its objectives.

8. <u>**Capital**</u>

The authorized capital of the Group is Birr 80,000,000,000 (Eighty Billion) of which Birr 20,000,000,000 (Twenty Billion) is paid up in kind.

9. <u>**Liability**</u>

The Group shall not be liable beyond its total assets.

10. <u>**Financial Year**</u>

The financial year of the Group shall be the Ethiopian government fiscal year that begins on Hamle 1st and ends on Sene 30th of the Ethiopian calendar.

11. <u>**Books Of Account**</u>

The books of account and audit of the Group governed in accordance with a Proclamation to provide for Financial Reporting No. 847/2014.

**፲፪. ቆይታ**

ግሩፑ የተቋቋመው ላልተወሰነ የጊዜ ቆይታ ነው፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ስለ መከላከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከል**

**፲፫. መቋቋም**

፩/ የመከለከያ ዲያግኖስቲክ ማዕከል (ከዚህ በኋላ “ማዕከል”) እየተባለ የሚጠራ የመንግስት የልማት ድርጅት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ማዕከሉ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮ መሰረት ይተዳደራል፡፡

**፲፬. ተጠሪነት**

የማዕከሉ ተጠሪነት ለግሩፑ ይሆናል፡፡

**፲፭. ዋና መስሪያ ቤት**

የማዕከሉ ዋና መስሪያ ቤት ቢሾፍቱ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም የሀገሪቱ ክፍል ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፲፮. የማዕከሉ ተግባርና ኃላፊነት**

በአዋጁ ለመንግስት የልማት ድርጅት የተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማዕከሉ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ዘመናዊ የዲያግኖስቲክ መሳሪያዎችን እና ብቃት ያለው የሰው ሃይል በመጠቀም ምርመራዎችን ማድረግ እና የሚመራበትን የአሰራር ስርአት መዘርጋት፤

፪/ በሀገር ውስጥ ገበያ የማይገኙ ለማዕከሉ ተግባር የሚውሉ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን በቀጥታ ከውጭ ገዝቶ ማስገባት፤

**12. Duration**

The Group is established for indefinite period.

**SUB SECTION TWO**

**Defence Diagnostic Centre**

**13. Establishment**

1/ Defense Diagnostic Center (hereinafter referred to as "The Center") is hereby established by this Regulation as a Federal Public Enterprise.

2/ The Center shall be governed by the Federal Government -Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024.

**14. Supervising Authority**

The Group shall be the supervising authority of the Centre.

**15. Head Office**

The Centre shall have its Head Office in Bishoftu and it may open branches in other parts of the country as may be necessary.

**16. Duties and Responsibilities of the centre**

Without prejudice to the duties and responsibilities of Public Enterprise provided in the Proclamation, the center shall have the following duties and responsibilities:

1/ By using modern diagnostic equipment and qualified personnel carry out examinations and establish a management system;

2/ Purchase and import goods and services that are not available in the domestic market for the Centre;

፫/ የገበያ መርህን እና አለማቀፍ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን መቅጠር፤ ክፍያ እና ማበረታቻዎችን መወሰን፤

፬/ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ምንጮች ገንዘብ የመሰብሰብ ፤

፭/ ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ፣ የመከራየት፣ የማከራየት፣ እና የመጠቀም፤

፮/ የኢንቨስትመንት አዋጭነትን እና የሽርክና ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት፤

፯/ ሌሎች የማዕከሉ ዓላማዎችን ለመወጣት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ይፈፅማል፡፡

፲፯. **<u>ካፒታል</u>**

የማዕከሉ የካፒታል መጠን ብር ፮ ቢሊዮን (ስድስት ቢሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን) በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፲፰. **<u>ሀላፊነት</u>**

ማዕከሉ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፲፱. **<u>የሂሳብ ዓመት</u>**

የማዕከሉ የሂሳብ ዓመት የኢትዮጵያ መንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን ከሐምሌ አንድ ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ሠላሳ ቀን የሚቆጠር ይሆናል፡፡

፳. **<u>የሂሳብ መዝገብ አያያዝ</u>**

የማዕከሉ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና ኦዲትን በተመለከተ በየፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ መሰረት ይመራል፡፡

3/ Employ appropriate staff, determine their payment and incentives in accordance with commercial principles and international best practice;

4/ Raise money from local and foreign source;

5/ Purchase, sell, rent, lease, and utilize immovable and movable properties;

6/ Investigate and make decisions on the investment feasibility, capital levels, and partnership issues;

7/ To engage in any other activities that is necessary for the attainment of its objectives.

17. **<u>Capital</u>**

The authorized capital of the center is Birr 6,000,000,000 (Six Billion) of which Birr 1,500,000,000(One Billion Five Hundred Million) is paid up in kind.

18. **<u>Liability</u>**

The center shall not be liable beyond its total asset.

19. **<u>Financial Year</u>**

The financial year of the center shall be the Ethiopian government fiscal year that begins on Hamle 1st and ends on Sene 30th of the Ethiopian calendar.

20. **<u>Books of Account</u>**

The books of account and audit of the center is governed in accordance with a Proclamation to provide for Financial Reporting No. 847/2014.

፳፩. **ቆይታ**

ማዕከሉ የተቋቋመው ላልተወሰነ የጊዜ ቆይታ ነው፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

፳፪. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እንዲሁም ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት የለውም፡፡

፳፫. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም።**

**ዐብይ አህመድ አሊ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

21. **Duration**

The Center is established for indefinite period.

**PART THREE**

**Miscellaneous Provisions**

22. **Inapplicable Laws**

Any Regulation, Directives or customary practice that contravene with this Regulation is not applicable.

23. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on this 4th day of March /2025.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**